**በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና**

**ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ የመኖሪያ ቤት መግዣ/መስሪያ**

**የቁጠባ ሂሣብ እና ብድር**

# Diaspora Mortgage Saving Account and Mortgage Loan

## 1. አጠቃላይ ይዘት

- ይህ ሂሣብ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት መግዣ/መስሪያ ብድር ከባንኩ እንዲያገኙ የሚያስችል የብር የቁጠባ ሂሳብ ነው፡፡
- ወደዚህ ሂሣብ ገቢ ማድረግ የሚቻለው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የውጭ አገር ገንዘቦች ብቻ ነው፤
  - ✓ የአሜሪካን ዶላር
  - ✓ የእንግሊዝ ፓውንድ
  - ✓ ዩሮ
- ከውጭ አገር የተለያዩ የገንዘብ ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም ወደ ተከፈተው ሂሣብ ገንዘብ በቀጥታ ገቢ ማድረግ ይቻላል፡፡
- በጥሬ ገንዘብ ገቢ ለማድረግ የውጭ ምንዛሪው ወደአገር ሲገባ በጉምሩክ በኩል የተመዘገበበትን የገንዘብ ዲክላራሲዮን በማስረጃነት ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡
- ወደተከፈተው ሂሣብ ተቀማጭ የሚሆነው ገንዘብ በዕለቱ ባለው የውጭ ምንዛሪ መጠን ተሠልቶ ወደ ብር ተቀይሮ ተቀማጭ ይሆናል፡፡
- በዚህ ሂሣብ ላይ መደበኛው የተቀማጭ ሂሣብ የወለድ መጠን ይከፈላል፡፡
- ከዚህ ሂሣብ በማንኛውም ጊዜ በብር በከፊል ወይም በሙሉ ወጪ ማድረግ ይቻላል፡፡

## 2. የብቁነት መስፈርቶች

የዚህ ሂሣብ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት፣

- ➢ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣
- ➢ በውጭ አገር የሚኖሩ በትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች፣
- ➢ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ነገር ግን በሥራ ምክንያት በውጭ አገር ከአንድ ዓመት በላይ የኖሩ እና የሚኖሩ ለዚህም በቂ ማስረጃ ሊያቀርቡ የሚችሉ ናቸው፡፡

## 3. ሂሳቡን ለመክፈት የሚስፈልጉ ሠነዶች

- በትክክል የተሞላ እና በሂሣብ ከፋቹ ወይም በወኪሉ የተፈረመ የሂሳብ መክፈቻ ማመልከቻ ቅጽ፣

  To download the form Click here
- ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊነት ፓስፖርት፣
- በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ዜግነት የወሠዱበት አገር ፓስፖርት እና የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ፣
- የመኖሪያ ወይም የሥራ ፈቃድ፣
- የሂሳብ ከፋቹ አንድ የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ፣
- ሂሳቡ በወኪል የሚከፈት ከሆነ የተወካዩ ፎቶግራፍ፡ የውክልና ሰነድ እና የመታወቂያ ካርድ ናቸው።

**4. የሂሳቡ አከፋፈት ሁኔታ**

- በግንባር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች በመቅረብ፣
- በግንባር መቅረብ የማይችሉ አመልካቾች ማንነታቸውን ለማረጋገጥ በያሉበት አገራት ባሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቆንጽላ ጽ/ቤቶች፣
- ህጋዊ የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች በመቅረብ በወካያቸው ስም ይህንን ሂሣብ መክፈት ይችላሉ፡፡

**5. በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ የመኖሪያ ቤት መግዣ/መሥሪያ ብድር (Diaspora Mortgage Loan) አጠቃላይ ይዘት**

- ይህ ብድር ለመኖሪያ ቤት መግዣ/መስሪያ የሚውል ነው፡፡
- ማንኛውም ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ዳያስፖራ የብድር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
- የብድር ጥያቄ ሲቀርብ አመልካቹ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ወይም መግዣ ዋጋውን ቢያንስ 20 በመቶ በውጭ ምንዛሪ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
- ባንኩ የሚሰራውን ወይም የሚገዛውን የመኖሪያ ቤት ዋጋ እስከ 80 በመቶ ያበድራል፡፡
- ብድሩ በአሜሪካን ዶላር÷ በእንግሊዝ ፓውንድ ወይም በዩሮ መከፈል ይኖርበታል፡፡
- የብድር ጥያቄ ሲቀርብ የሚከተሉት ሰነዶች መሟላት ይኖርባቸዋል፤
    - ➢ የመኖሪያ ወይም የሥራ ፈቃድ፣
    - ➢ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊነት ፓስፖርት፣
    - ➢ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ዜግነት የወሠዱበት አገር ፓስፖርት እና የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ፣
    - ➢ ሁለት የቅርብ ጊዜ ፎቶግራፍ፣
    - ➢ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ወይም ያላገባ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ፣
    - ➢ ብድሩ የተጠየቀው በወኪል አማካይነት ከሆነ የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ኮፒ፣ ሁለት የቅርብ ጊዜ ፎቶግራፍ እና የውክልና ሰነድ ማስረጃ፣
    - ➢ እንደአስፈላጊነቱ ጠቅላላ ዓመታዊ የደመወዝ መጠን እና የተጣራ ገቢን የሚገልጽ ከቀጣሪ የተሰጠ የቅጥር ደብዳቤ፣
    - ➢ እንደአስፈላጊነቱ የቅጥር ውል ኮፒ፣
    - ➢ ከውጭ አገር ባንክ ቢያንስ የአንድ ዓመት የሂሳብ መግለጫ፣
    - ➢ አመልካች በንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል፤
        - ቢያንስ የሦስት ተከታታይ ዓመታት ዝርዝር የሂሳብ መግለጫ፣
        - የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት እና
        - የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት፣
    - ➢ የብድር መክፈያ ጊዜ ከ20 ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡
    - ➢ ለብድሩ የሚከፈለው የወለድ ምጣኔ በዓመት ቢያንስ 8.5 በመቶ ይሆናል፡፡

http://www.ethiopianembassy.org/Community/DiasporaLoanFormRevised.pdf